# *ሰሞነኛ*

# በሎስአንጀለስ የኢትዮጵያ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት

**ህዳር/1999**

November /2006




**Consulate**

**General of Ethiopia**

**3460 Wilshire Blvd # 308**

**Los Angeles,CA 90010**

**Tel: 213 365 6651**

**Fax:213 365 6670**

**www.ethioconsulate-la.org**


## በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ አሁንም የሀገሩ ልማት ዓለኝታ ነው፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ዙሪያ መለስ የሆነ የኢኮኖሚ ማህበራዊና ፖለቲካዊ የችግር አዙሪት ውስጥ የሚገኙ ሀገሮች ሁሉንም የኢኮኖሚና ማህበራዊ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎችን ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡ይህን አመለካከት ተግባራዊ ለማድረግ በግንባር ቀደም ከሚጠቀሱት የልማት ኃይሎች አንዱ ደግሞ በውጭ የሚገኙ ወገኖቻችን ናቸው፡፡

በተለያዩ ምክኒያት ከውድ ሀገራቸው ወጥተው በዩናይትድስቴትስ የሚኖሩ ኢትዮጵውያን በአገር ቤት በልዩ ልዩ የንግድና ኢንቨስትመንት እንዲሁም የግብረ-ሰናይ ተግባራት ተሰማርተው ሀገራቸውንና ወገናቸውን በማገልገል ላይ ይገኛ ሉ፡፡የዘመዶቻቸውን መጠለያ ቤት የሚገነቡ የሚጠግኑና የሚያሻሽሉ እንዲሁም ደካማ ወገኖቻቸውን በሚልኩት የገንዘብ ትሩፋት የሚታደጉ ጥቂት ሳይሆኑ አጅግ እልፍ ናቸው፡፡

እነዚህ ከአካባቢያችን የሄዱ ወገኖች ድንግል መሬት አርሰው ወንዝ ቀልብሰውና በርሀማ የአየር ሙቀትን ተቋቁመው ሰሊጥና ጥጥ አምርተው ለውጭ ገብያ ሲያቀርቡ ማየት ታላቅ ተፍስሂት ነው፡፡በአዲስአበባ ባህርዳር መቀሌ አዋሳ ጎንደር ድሬድዋ ናዝሬት ጅማና በሌሎች ትንንሽ የሀገራችን ከተሞች ሳይቀር በሚታየው ሁለገብ የግንባታ ሥራ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ድርሻ የጎላ ሆኗል፡፡

በሎስ አንጀለስ በሳንሆዜ ኦክላንድ ሲያትል ዴንቨር እና ሳንዲያጎ ወደ ሀገር ቤት የተመለሱ ኢትዮጵያውያን ወገኖች በዘመናዊ ህንፃ ሥራ በሆስፒታልና በት/ቤት ግንባታ በአበባና በእንሰሳት ሀብት ምርት እንዲሁም በኮንስትራክሽን መሳሪያዎች አቅርቦትና በኤክስፖርት ኢምፖርት የንግድ ሥራ

ተሰማርተው በርካታ የሥራ ዕድል በመፍጠር የሀገርና የወገን አለኝታ በመሆን ላይ ይገኛሉ፡፡

በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ይህን ተግባር የሚያከናውኑት በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ አገራቸውንና ወገናቸውን ጠቅመው እራሳቸውን ለመጥቀም እንደሆነ እሙን ነው፡፡ከሁሉም በላይ በዚህ በውጭ ሀገር እልህ አስጨራሽ በሆነና ዕረፍት በሌለው የሥራ መስክ ተሰማርተው የሚያገኙትን ገንዘብ አጠራቅመውና ቋጥረው ሲሆን የተለያዩ ራስን ሊፈታተኑ የሚችሉ አመለካከቶችን ሰምተው እንደ አልሰሙ ሆነው በስራ ላይ የሚታዩት ሀገር ለምታና ተለውጣ ለማየት ካላቸው ፅኑ ፍላጎት ስለሆነ ሊወደሱ ሊደገፉና ሊበረታቱ ይገባል፡፡

ውድ ሀገራችን ከድህነት አረንቋ ለማውጣት የህዝባችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የሚቻለው ትንሽም ይሁን ትልቅ እየአንዳንዳችን በልማት በንግድ በግብረ ሰናይ በትምህርትና በዕውቀት ሽግግር መስክ የበኩላችን አስተዋፅኦ ስናደርግ ነው፡፡በዚህ ዙሪያ ቀደምት ዕርምጃ የወሰዱ ኢትዮጵያውያንን አርአያ በማድረግ እንዲሁም የህዝባችንን ዕድገት ተስፋና ተነሳሽነት ግምት ውስጥ በማስገባት ራሳችንን ጠቅመን ህዝባችን እንታደግ እንላለን፡፡

## የኢትዮጵያ ሚሊኒየም አንዱ ብርቅየ የኢትዮጵያ ታሪክ መገለጫ፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትታወቅባቸው በርካታ ድንቅና ብርቅ የሆኑና በሌሎች ቦታዎች የማይገኙ ዕፅዋት እንሰሳትና የተፈጥሮ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጦች ባለቤት ናት፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን የተለያዩ መንፈሳዊ ዕምነቶችና ትውፊቶች ባሌቤት መሆኗ ብዙዎችን ሲያስደምም ይታያል፡፡በተለይም ከክርስትናና እስልምና ዕምነቶች ጋር ተያይዘው የሚታዩት የበአላተ አከባበሮች፣ የደስታና የሀዘን መግለጫ የሆኑ ዜማዎችንና ግጥሞች ከብዙ ጥቂቶች ናቸው፡፡

በአገራችን ከሌላው ዓለም የተለየ የሰዓት የቀንና የዘመን አቆጣጠር መኖር ከብርቅየ የመገለጫ ሀብቶቻችን አንዱ ነው፡፡ ለአብነት ያህል፣ 12ቱ ወሮች እኩል 30 ቀናት ያላቸው ሲሆን 13ኛ ወር ጳጉሜ 5 ቀናትና በ4ኛው አመት 6 ቀናት እንዲኖራቸው ተደርጎ የተሰራበት ሥርአት ነው፡፡ለዚህም ነው ሀገራችን ለማስተዋወቅ የፈለጉ ተቋማትም፡ ይሁን የዜማ ሰዎች ኢትዮጵያ የ13 ወር ፀጋ ያላት ሀገር ነች ሲሉ የሚደመጠው፡፡

የኢትዮጵያ ቀን አቆጣጠር ከፈረጆቹ ቀን አቆጣጠር ከ7 እስከ 11 ቀን በተለያዩ የዓመቱ ወራት የሚለያይ ነው፡፡ የዓመት አቆጣጠራችንም ከጥር በፊት በ7 ዓመት ከጥር በኃላ በ8 ዓመት ከፈረጆቹ የዓመታት አቆጣጠር ይለያል፡፡

ይህንኑ መነሻ በማድረግም የፈረንጆች ሚሊኒየም ከተከበረ 6 ዓመታት ያለፉት ቢሆንም የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ግን ሊከበር 8 ወራት ይቀሩታል፡፡ ይህን የተለየ የዕልፍ ዘመን አቆጣጠር በመንተራስ በሀገር ቤት የሚገኙ ወገኖቻችን ልዩ ልዩ የበዓል ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

በዓሉ የፌስታና የፈንጠዝያ ሳይሆን ሀገራችን ከድህነት ለመውጣት ምታደርገውን እንቅስቃሴ መሰረት በማድረግ ዜጎች ቁርጠኝነታቸውን የሚያድሱበት በመከባበር በመቻቻልና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲአዊ ፖለቲካዊ አንድነት የሚጠናከርበት ዘመን እንዲሆን ታስቦ የሚከናወን በዓል ነው፡፡

በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንም ይህን ሚሊኒየም በዓል መነሻ አድርገው የሀገራቸውን የተለያዩ ሀብቶች ሌሎችም እንዲያውቁት በማድረግ እንዲሁም እነሱም ሊኮሩባት ሊንከባከቧትና ሊያለሟት የሚገባ ሀገር እንዳላቸው ፅኑ ዕምነት ይይዙበታል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ስለዚህም ይህን የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ታሪክ ወዳድና ሀገር ጎብኚ የውጭ ሰዎች ተገኝተው በበዓሉ በመታደም የሀገራችንን ውብ ሀብቶች በመመልከት በርሀብና በዕርዛት ብቻ የሚያውቁንን አከላት አመለካከት መለወጥ ወገናዊ ድርሻ ነው፡፡

በተለይም በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ቤት የምናደርገውን ጉብኝት በነዚህ ወራት በማድረግ አዲሱን የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ከወገኖቻችን ጋር ለማክበር ከአሁኑ ዝግጅት እንድናደርግ እየጠቆምን የሎስአንጀለስ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት በዚህ ረገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ይገልፃል፡፡